የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ–የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 35
ADDIS ABABA - 9th February 1999

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፭/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
ለሦስተኛው የትምህርት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፱፻፹፩

CONTENTS

Proclamation No. 155/1999
African Development Fund Loan Agreement for financing the Education III Project Ratification Proclamation ........................................ Page 981

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፭/፲፱፻፺፩
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለሦስተኛው የትምህርት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ዩ.ኤ. ፴፪ ሚሊዮን (ሠላሳ ሁለት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የትምህርት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፭/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 155/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of UA 32,000,000 (thirty two million Units of Account) for financing the Education III Project, was signed in Abidjan on the 20th day of November, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 9th day of February, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for financing the Education III Project Ratification Proclamation No. 155/1999."

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·አ·አ ኖቬምበር ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢ·ቲኤች/ኢ·ዲዩ – ፫/፺፰/፵ የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ·ኤ·፴፪ ሚሊዮን (ሠላሳ ሁለት ሚሊዮን ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፣ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. F/ETH/EDU-3/98/40, signed in Abidjan on the 20th day of November, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the loan amount of UA 32,000,000 (thirty two million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 9th day of February, 1999.

Done at Addis Ababa, this 9th day of February, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESDIENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE